
ArdaghGroup

# የሥነ ምግባር
# ደንብ

የንግድ ሥራን በትክክለኛው መንገድ
ለመሥራት ሁልጊዜም ጊዜው ነው



ቀን፦ ታህሳስ 2025

እትም፦ 6.0

# ይዘቶች


መልዕክት ከሊቀመንበር እና ከዋና ስራ አስፈጻሚዎች....3

ዓላማችን እና ዋነኛ እሴቶቻችን....4
- ዓላማችን....4
- መሠረታዊ እሴቶቻችን....5

የንግድ ሥራን በትክክለኛው መንገድ መሥራት..6
- የሥነ-ምግባር ደንባችን ምንድነው?....6
- ደምቡ ተፈጻሚ የሚሆነው በማን ላይ ነው?7
- ኃላፊነቶቻችን....7
- የአስተዳዳሪ ኃላፊነቶች....8
- ማዕቀቦች....9
- ከደንቡ ውጭ የሚሰራባቸው ሁኔታዎች....9
- እርዳታ ማግኘት....9
- መናገር....10

ለሰራተኞቻችን እና ለደህንነታችው ዋጋ እንሰጣለን....11
- የሥራ አካባቢ ጤና እና ደህንነት....11
- በሥራ ላይ ያሉ መሠረታዊ መብቶች....13
- ብዝኀነት፣ እኩልነት እና አካታችነት....14
- መከባበር ያለበት የሥራ አካባቢ....14

ሥራዎቻችንን በሥነ ምግባር እና በሐቀኝነት እንሠራለን....16
- ጉቦም ሆነ ሙስና አይፈቀድም....16
- ስጦታዎች እና መስተንግዶ....18
- የጥቅም ግጭቶች....20
- የኮርፖሬት መልካም ዕድሎች....21
- ትክክለኛ የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ....21
- ውስጥ አዋቂ የአክሲዮን ግብይት....23
- የውድድር እና የጸረ-ውድድር ሕጎች ተሰማሚነት....25
- ማዕቀቦች እና ወደ ውጭ የመላክ ክልከላ ሕጎች....26

የንግድ ሥራችንን እንጠብቃለን....27
- ማጭበርበርን መከላከል....27
- ተጨባጭ ንብረቶቻችንን ደህንነት መጠበቅ....28
- ምስጢራዊ መረጃዎቻችንን መጠበቅ....29
- የመረጃ ቴክኖሎጂ (IT) ሥርዓቶቻችንን መጠበቅ....30
- የመረጃ ግላዊነት....31

ለአካባቢያችን እና ለማህበረሰባችን እንጨነቃለን32
- ለአካባቢያችን ዋጋ መስጠት....32
- ዘላቂነት ላይ ማተኮር....33
- ማህበረሰባችንን መደገፍ....34
- በእሴት ሰንሰለታችን ውስጥ ሰብዓዊ መብቶችን ማክበር እንዲሁም የማኅበራዊ ኃላፊነቶች መከበርን ማስፋፋት....35

የመረጃ ምንጮች....36




ዓላማችን እና ዋነኛ እሴቶቻችን | የንግድ ሥራን በትክክለኛው መንገድ መሥራት | ለሰራተኞቻችን እና ለደህንነታችው ዋጋ እንሰጣለን | ሥራዎቻችንን በሥነ ምግባር እና በሐቀኝነት እንሠራለን | የንግድ ሥራችንን እንከላከላለን | ለአካባቢያችን እና ለማኅበረሰቦች እንጨነቃለን | የመረጃ ምንጮች

# መልዕክት ከሊቀመንበር እና ከዋና ስራ አስፈጻሚዎች

እኛ በአርዳ ያለን፣ ሥነ ምግባር እና ታማኝነት በተሟላ መንገድ እንዲሁም ተፈጻሚነት ያላቸውን ሁሉንም ሕጎች በማክበር ለመሥራት ቁርጠኞች ነን።

የሥነ-ምግባር ደንባችን የተዘጋጀው ለሥራችን እና ከእኛ ጋር ለሚሰሩ ሁሉ መመሪያ ሆኖ እንዲያገለግል ነው። እርስ በርሳችን፣ ከደንበኞቻችን ጋር፣ እንዲሁም ከአቅራቢዎች እና ባለ ድርሻ አካላት ጋር ለሚኖረን መስተጋብር ማዕቀፍ የሚያስቀምጥ ነው። በተለይም፣ የሥነ-ምግባር ደንባችን በዓላማችን ዙሪያ የተገነባ ነው፦ “We make packaging for good” እና አካታችነት፣ መተማመን፣ የቡድን ሥራ እና ልዕቀት የተባሉት ዋነኛ እሴቶቻችን።

የሥነ ምግባር ደንባችን በሁሉም ሰራተኞቻችን ላይ ተፈጻሚ ይሆናል። የሥነ ምግባር ደንቦችን ማንበብ እና መከተል የሁሉም ሰራተኛ ኃላፊነት ነው። የራስዎን ወይም የሌላን ሰው ተግባር በተመለከተ ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች ካሉብዎ፣ ድምጽዎን እንዲያሰሙ እና ስጋቶችዎን እንዲያጋሩ እናበረታታዎታለን። በመጀመሪያው ገጠመኝዎ ለቅርብ ሃላፊዎ ስለ ጉዳዩ ማሳወቅ አለብዎ። እንደ አማራጭም፣ ስጋትዎን ለመንገር፣ Group Legal & Compliance (የግሩፕ ህግ እና ተሰማሚነት) አባልን ማነጋገር ይችላሉ፤ እንዲሁም Speak-Up Hotline (በድምጽዎን ያሰሙ የቀጥታ መስመር) ማንነትዎን ሳያስውቁ ስጋትዎን መናገር ይችላሉ።

በሥነ-ምግባር ደንቦቻችን መሰረት መስራት፣ ሁላችንም የምንኮራበት እና፣ ቀጣይነት ያለንን ቁርጠኝነት እንዲሁም አንዳችን ለሌላችን ያለንን አክብሮት የሚያንጸባርቅ የንግድ ሥራ መገንባታችንን እንድንቀጥል ይረዳናል።



**Mark Porto**
Executive Chairman of Ardagh Holdings S.A.

**Oliver Graham**
Chief Executive Officer Ardagh Metal Packaging

**Mike Dick**
Chief Executive Officer Ardagh Glass Packaging

# ዓላማችን እና ዋነኛ እሴቶቻችን

እሁን ያለንበት የንግድ ሁኔታ በየግዜው የሚቀያየር ነው። ነው። ይሁን እንጂ፣ የማይቀየረው ለዓላማችን እና ለመሰረታዊ እሴቶቻችን ያለን ቁርጠኝነት እንው። እነዚህ፣ እኛ እንደ ኩባንያ ማን እንደሆንን የሚወሰኑ ከመሆኑም በላይ ለንግድ ሥራችን መሰረት ናቸው። ለደንበኞቻችን፣ ለአቅራቢዎቻችን፣ ለባለ ድርሻ አካላት፣ እንዲሁም እርሰበርሳችን ላለን መከባበር ያለንን ቁርጠኝነት የሚያሳዩ ናችው።

ስራተኞቻችን የሚጋሩት ከጠንካራ ጥራት መለያችን እና ከፍ ካለ ዝና በላይ ነው። እያንዳንዳችን የጋራ ዓላማ እንጋራለን - We make packaging for good። ዓላማችን የደንበኛ ፈጠራን እንድናሰረክብ፣ ለቡድኖቻችን አነቃቂ የሥራ አካባቢ እንድናቀርብ፣ የንግድ ሥራችንን ወደ እድገት እና ልማት እንድንመራ ያስችለናል።

የምንፈጥረው መጪ ጊዜ የሚገነባው በአራቱ መሠረታዊ እሴቶቻችን፣ አካታችነት፣ መተማመን፣ የቡድን ሥራ እና ልዕቀት ዙሪያ ነው። እንቅስቃሴዎቻችንን በከፍተኛ የሐቀኝነት ደረጃ ለማከናወን ቁርጠኞች ነን።






ዓላማችን እና ዋነኛ እሴቶቻችን | የንግድ ሥራን በትክክለኛው መንገድ መሥራት | ለሰራተኞቻችን እና ለደህንነታችው ዋጋ እንሰጣለን | ሥራዎቻችንን በሥነ ምግባር እና በሐቀኝነት እንሠራለን | የንግድ ሥራችንን እንከላከላለን | ለአካባቢያችን እና ለማኅበረሰቦች እንጨነቃለን | የመረጃ ምንጮች

# መሠረታዊ እሴቶቻችን

## አካታችነት

አካታችነት ማለት የሌሎችን መኖር ልብ እንላለን፣ ሁሉም ሰው አስተዋጽዖ እንዲያደርግ እናበረታታለን፣ እንዲሁም ለሐሳብ ብዝሃነት ዋጋ እንሰጣለን። በሥራ ላይ ስንሆን፣ ሁላችንም ምቾት ሊሰማን እና እራሳችንን ሆነን በራስ መተማመን ሊሰማን ይገባል።

## መተማመን

መታመን የሚገኘው አክባሪ፣ እምነት የሚጣልብን፣ ወጥ ባህሪ ያለን፣ እና ሌሎችን በቅንነት የምንቀርብ መሆናችንን የሚያመለክቱ ጠባዮችን ስናሳይ ነው። የሚገነባው ከሁሉም ወገን በሚወጣ መከባበር፣ የግል ባህሪ ወጥነት እና ግልጽነት ነው።

## የቡድን ሥራ

የቡድን ሥራ የሚሳካው በትብብር በመሥራት እና በተግባቦት ነው። እንደ አንድ ቡድን መሥራት፣ የአደጋ ሥጋቶችን እንድንለይ፣ የሥራ ላይ ደህንነትን ጠብቀን ለመሥራት እና የአደጋ ክስተቶችን ለመቀነስ ያስችለናል። ቡድኖች የእነርሱ ውሳኔዎች በሌሎች ቡድኖች ላይ የምኖራቸውን ተጽዕኖ ልብ ሊሉ ይገባል።

## ልዕቀት

ልዕቀት ማለት በትምህርት እና በልማት እራሳችንን ያለማቋረጥ በማሻሻል፣ እንዲሁም የንግድ ሥራውን ወደ ታላቅ ከፍታ ለማድረስ ያለን ቁርጠኝነት ነው።



አካታችነት | መተማመን | የቡድን ሥራ | ልዕቀት

# ሥራን በትክክለኛው መንገድ መሥራት

## የሥነ-ምግባር ደንባችን ምንድነው?

እኛ ሥራችንን ከፍተኛ ደረጃ ባለው ሐቀኝነት እና ታማኝነት ለመሥራት፣ እንዲሁም ሁሉንም ተፈጻሚነት ያላቸው ሕጎች እና ደንቦች በሁሉም በንግድ ሥራችን ውስጥ ባሉ እና ከሌሎች (ደንበኞችን፣ አቅራቢዎችን እና የመንግስት ባለሥልጣን መስሪያቤቶችን ጨምሮ)፣ እንዲሁም ሥራችንን ከምናከናውንበት ማኅበረሰብ ጋር ያሉን ግንኙነቶች ላይ በማክበር እና በመስማማት ለመሥራት ዝግጁ ነን። የሥነ-ምግባር ደንባችን (የእኛ "ደንብ") ይህን ቁርጠኝነት ለማሳካት የተዘጋጀ ማዕቀፍ ሲሆን፣ ተቀባይነት ያላቸው ባሕርያት ናቸው ብለን የምንወስዳቸውን በተመለከተ መርኆዎችን እና የሚጠበቁ ነገሮችን በግልጽ ያስቀምጣል።

በደንባችን ውስጥ ያሉ መርኆዎች ሁሉን-አካታች እንዲሆኑ ታስበው የተዘጋጁ አይደሉም፣ ይሁን እንጂ መሰረታዊውን የንግድ ሥራ አሰራር መንገዳችንን ለማመልከት አስፈላጊውን መመሪያ ያቀርባሉ። በደንባችን በሙሉ፣ ተያያዥ ቁልፍ ፖሊሲዎች ሲጠቀሱ ያያሉ። ከእነዚህም በተጨማሪ፣ ሌሎች ፖሊሲዎች እና መመሪያዎች የኮዳችንን መርኆዎች ይደግፋሉ ወይም ያስፈጽማሉ። እንዲህ አይነቶቹ ማናቸውም ፖሊሲዎች እና መምሪያዎች፣ በቡድን፣ በኩባንያ፣ ወይም በአካባቢያዊ ደረጃ የተሰጡ ቢሆኑም፣ በኢንትራኔታችን፣ የእኔ አርዳ በኩል የሚገኙ ሲሆን፣ እነርሱን መከተል ይገባል።

ኮዳችን፣ ሥራን ደንብ በማክበር፣ በታማኝነት፣ እና በፕሮፌሽናል መንገድ ለመሰራት እንደ መምሪያ መወሰድ አለባቸው፣ እንዲሁም ሁሉንም የንግድ ሥራ ውሳኔዎች ለማሳለፍ እርምጃዎችን ለመውሰድ እነርሱ ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው። ይህን በማድረግ፣ የንግድ ሥራችንን እናጠናክራለን፣ በመሠረታዊ እሴቶቻችን ላይ የተመሰረተ ባህል እንገነባለን፣ እንድሁም ንግድ ሥራን በትክክለኛው መንገድ እየሰራን መሆናችንን እናረጋግጣለን።



ሥራችንን ከፍተኛ ደረጃ ባለው ሐቀኝነት እና ታማኝነት ለማከናወን ቁርጠኞች ነን።





# ሥራን በትክክለኛው መንገድ መሥራት


## ደምቡ ተፈጻሚ የሚሆነው በማን ላይ ነው?

በንግድ ሥራችን ውስጥ ባለ ማንኛውም ሰው፣ በአርዳ ዳይሬክተሮች፣ መኮንኖች፣ በሁሉም ዓለማቀፍ አረዳ ግሩፕ ኩባንያዎቻችን እና ማናቸውም በአርዳ ቁጥጥር የሚደረግባቸው የሽርክና ሥራዎች ውስጥ በሚሰሩ በዓለም ዙሪያ ያሉ ሰራተኞች (በአጠቃላይ "ሰራተኞች") ላይ ተፈጻሚ ይሆናል። በተጨማሪም ሁሉም የንግድ አጋሮቻችን በኮዳችን ውስጥ የተቀመጡ መርኆዎችን እና እሴቶችን እንዲያከብሩ እንጠብቃለን። ደንባችን ሁሊጊዜም በአርዳ ቅጥር ግቢ ውስጥ፣ የአርዳን ተግባራት በምናከናውንባቸው ከቅጥር ውጭ የሆኑ አካባቢዎች፣ ወይም አርዳን ወክለን በምንንቀሳቀስባቸው ሁሉም ቦታዎች ተፈጻሚ ይሆናል።

## ኃላፊነቶቻችን

ኮዳችንን በማንበብ እና በማክበር፣ ከፍተኛ የሐቀኝነት ደረጃን ለማሟላት ሁላችንም ኃላፊነት አለብን። በኮዳችን ውስጥ የተቀመጡ መርኆዎችን እና እነርሱን የሚተገብሩ ማናቸውንም ፖሊሲዎች መረዳትዎን ማረጋገጥ አለብዎ። ካልተረዱ፣ ማብራሪያ ከፈለጉ፣ ወይም እርስዎ የወሰዱት እርምጃ ትክክለኛነቱ ካጠራጠረዎ፣ ከቅርብ ኃላፊዎች ከሰው ኃይል አስተዳደር ኃላፊ ወይም ከGroup Legal & Compliance እገዛ ይጠይቁ። ኮዳችንን የሚጥስ ወይም ከእርሱ ጋር የማይስማማ ድርጊት ከተመለከቱ ወይም መኖሩን ከተጠራጠሩ፣ ወዲያውኑ መናገር አለብዎ።

በተጨማሪም በእርስዎ ንግድ ሥራ ላይ ተፈጻሚነት ያላቸውን ሕጋዊ እና ደንባዊ መስፈርቶች ማወቅ እና ተግባርና ኃላፊነቶችዎንም በእነርሱ መሰረት ማከናወን ይጠበቅብዎታል። የማናቸውንም ሕጎች እና ደንቦች ተፈጻሚነት የተመለከቱ ጥያቄዎች Group Legal & Compliance መቅረብ አለባቸው።



# ሥራን በትክክለኛው መንገድ መሥራት

## የአስተዳዳሪ ኃላፊነቶች

እርሰዎ ኃላፊ ከሆኑ፣ አርዓያ መሆን አለብዎ፣ ሁልጊዜም ለቡድንዎ መልካም ምሳሌ መሆንና በኮዳችን ውስጥ የተቀመጡ መርኆዎች ለማክበር ያለዎትን ቁርጠኝነት በቃልም ሆነ በተግባር ለቡድንዎ ማሳየት አለብዎ።

ኃላፊዎች በፍተኛ ደረጃ በሐቀኝነት የመሥራት ልዩ ኃላፊነት አለባቸው።

በሥነ-ምግባር ባህል መገንባት እና ቡድንዎ በመርኆዎቻችን መሰረት እንዴት መሄድ እንደሚገባው መረዳቱን ማረጋገጥ ይኖርብዎታል። ሰራተኞች ጥያቄዎችን ወይም ስጋቶችን ይዘው ወደ እርሰዎ በሚመጡ ጊዜ፣ ወዲያውኑ ምላሽ መስጠት አለብዎ፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ጉዳዮን ወደ የበላይዎ ማስተላለፍ አለብዎ። ሊወሰዱ ባሰቡት እርምጃ ትክክለኝነት ላይ እርግጠኛ ካልሆኑ ፣ ወይም ከሌላ ሰው አተያይ የሚጠቀሙ ከሆነ ሁልጊዜም እርዳታ መጠየቅ አለብዎ፤ ከሥነ-ምግባር ውጭ የሆኑ እና ከደንባችን ጋር የማይሄዱ ድርጊቶችን በሚመለከቱ ጊዜ ሁልጊዜም መናገር አለብዎ።





ዓላማችን እና ዋነኛ እሴቶቻችን | የንግድ ሥራን በትክክለኛው መንገድ መሥራት | ለሰራተኞቻችን እና ለደህንነታችው ዋጋ እንሰጣለን | ሥራዎቻችንን በሥነ ምግባር እና በሐቀኛነት እንሠራለን | የንግድ ሥራችንን እንከላከላለን | ለአካባቢያችን እና ለማኅበረሰቦች እንጨነቃለን | የመረጃ ምንጮች

# ሥራን በትክክለኛው መንገድ መሥራት

## ማዕቀቦች

ደንባችንን፣ ፖሊሲዎቻችንን እና ተፈጻሚነት ያላቸውን ሕጎች ማክበር አለመቻል የዲሲፕሊን እርምጃ ሊያስከትል ይችላል። እንዲህ አይነቱ እርምጃ ተፈጻሚነት ባለው ሕግ መሰረት የሚፈጸምሲሆን፣ ሥልጠና፣ ምክር፣ ከሥራ መሰናበትን ሊያካትት ይችላል። በተጨማሪም፣ የወንጀል ሕጎች ተላልፈው ከተገኙ፣ ለተገቢዎቹ የሕግ አስፈጻሚ አካላት ልናሳውቅ እንችላለን።

## ከደንቡ ውጭ የሚሰራባቸው ሁኔታዎች


ከደንባችን ውጭ መሰራት አስፈላጊ ሆኖ ሊገኝባቸው በሚችሉባቸው (የመኖር ዕድላቸው ኢምንት ነው) የኩባንያውን ጸሐፊ ማነጋገር ያስፈልጋል። አንድ ዳይሬክተር ወይም መኮንን ከደንብ ውጪ ለመሥራት ከተገደደ ቀድሞ አረዳ የአርዳግ ሆልዲንግስ ኤስ.ኤ. . የዳይሬክተሮች ቦርድ ፈቃድ ማግኘት አለበት።

## እርዳታ ማግኘት

ደንባችን በርካታ ሁኔታዎችን ይሸፍናል፣ ነገር ግን ሁሉንም የያዘ አይደለም። ደን ባችንን ለመረዳት ማናቸውም ድጋፍ ከፈለጉ፣ የቅርብ ኃላፊዎን ወይም የሰው ኃይል አስተዳደር ኃላፊ አባልን መጠየቅ አለብዎ። አሁንም ግልጽ ካልሆነልዎ፣ Group Legal & Compliance አባልን መጠየቅ ይችላሉ።

አንዳንድ ባህሪዎች እና ልማዶች ደንብ የሚያከብሩ መሆናቸውን ለማየት ሊጠይቋቸው የሚችሏቸው አንዳንድ ጥያቄዎች እነሆ፡-

- ሕጋዊ ነው?
- ከሥነ-ምግባር ደንባችን እና ፖሊሲዎች ጋር የሚስማማ ነው?
- ትክክል ይመስላል፣ እንዲሁም የትክክለኛነት ስሜት ይሰጣል?
- የእርሰዎን ወይም የእኛን መልካም ስም ሊያጎድፍ ይችላል?



ዓላማችን እና ዋነኛ እሴቶቻችን | የንግድ ሥራን በትክክለኛው መንገድ መሥራት | ለሰራተኞቻችን እና ለደህንነታችው ዋጋ እንሰጣለን | ሥራዎቻችንን በሥነ ምግባር እና በሐቀኝነት እንሠራለን | የንግድ ሥራችንን እንከላከላለን | ለአካባቢያችን እና ለማኅበረሰቦች እንጨነቃለን | የመረጃ ምንጮች

# ሥራን በትክክለኛው መንገድ መሥራት

## መናገር

ደንባችን፣ ፖሊሲዎቻችን ወይም ሕግ ሲጣስ ከተመለከቱ ወይም ከተጠራጠሩ፣ ወዲያውኑ መናገር በጣም አስፈላጊ ነው። በመጀመሪያ ጉዳዩን ለመስመር ኃላፊዎ ይንገሩ። በማንኛውም ምክንያት ይህን ለማድረግ ምቾት ካልተሰማዎ የሰው ኃይል አስተዳደርን ወይምGroup Lega & Compliance.  አባልን ማነጋገር ይችላሉ።

ሌላ ስጋቶችዎን ሪፖርት ማድረግ የሚችሉበት ቦታ “Speak-Up Hotline” በኩል ነው። Speak-Up Hotline መስመራችን በገለልተኛ ሶስተኛ ወገን የሚተዳደር ሲሆን ለሁሉም ሰራተኞች ስጋቶችን ምስጢራዊ በሆነ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ውጤታማ በሆነ አኳኋን ሪፖርት ለማድረግ ዕድል ይሰጣል። በአካባቢያዊ ሕጎች መሰረት፣ ሪፖርቶች ማንነትን ሳያሳውቁ ሊቀርቡ ይችላሉ። Speak-Up Hotline መስመራችን በመስመር ላይ ardaghgroup.ethicspoint.com እንዲሁም እኛ ሥራ በምናከናውንባቸው ሁሉም አገሮች ውስጥ በአገር ውስጥ የነጻ መስመር ቁጥሮች በኩል ይገኛል። Speak-Up Hotline መስመራችንን ማግኘትን በተመለከተ በዚህ ደንብ መጨረሻ ላይ ባለው የመረጃ ምንጮች ክፍል ውስጥ ተጨማሪ መረጃ Group Legal & Compliance መገኛ አድራሻን ጨምሮ ማግኘት ይችላሉ።

ሁሉንም ሪፖርት የሚደረጉ ስጋቶች የምር እንወስዳቸዋለን፤ እንዲሁም Speak-Up Hotline የምንቀበላቸው ጥቆማዎች ብቃታቸው በተረጋገጡ ባለሙያ መርማሪዎች ይያዛሉ።

*የበቀል እርምጃ አይኖርም*

መረጃን በቅን ልቡና፣ ይኸውም ማለት እውነቱን እርስዎ በተረዱበት መጠን ሪፖርት በማድረግዎ ምክንያት ማናቸውም አጸፋዊ እርምጃዎች እንዲወሰዱ አንፍቃድም። አጸፋዊ እርምጃ ወይም መድልዎ ይደርሰብኛል ብለው ሳይሰጉ፣ ይኸውም ማለት የዲሲፕሊን እርምጃ ይወሰድብኛል ወይም ከሥራ እሰናበታለሁ የሚል ስጋት ሳይኖርብዎ፣ ማናቸውንም ደንብ ወይም ማናቸውም ሌሎች ከሥነ-ምግባር ያፈነገጡ ተግባሮችን ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ።

**ተያያዥ ፖሊሲ:-**

ድምጽን የማሰማት እና የጥቆማ ፖሊሲ

የሥነ-ምግባር ደንባችን ተጥሷል ብለው ጠርጥረዋል? ለሚከተሉት መናገር ይችላሉ:-

- ለመስመር ኃላፊዎ
- ለሰው ኃይል አስተዳደር
- Group Legal & Compliance
- Speak-Up Hotline አማካኝነት



# ለሰራተኞቻችን እና ለደህንነታቸው ዋጋ እንሰጣለን

በሥራ አካባቢያችን ማናቸውም ሰራተኞች እና ሶስተኛ ወገኖች ደህንነታቸው የተጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ቁርጠኞች ነን። የእኛ የማምረቻ ተቋሞች፣ የአገልግሎት ማዕከላት እና ቢሮዎች፣ ሰዎች ወደ ሥራ ለመምጣት የሚጓጉላቸው፣ ከዚያም በደህና ወደየቤታቸው የሚመለሱባቸው፣ እንዲሁም ሁሉም ሰው በሚዛናዊነት እና በአክብሮት የሚስተናገድባቸው ቦታዎች መሆን አለባቸው።




## የሥራ አካባቢ ጤና እና ደህንነት

ደህንነት የሥራችን ዋነኛ አካል ነው። ለሁሉም ሰራተኞች ለጤና ተስማሚ እና ደህንነቱ የተጠበቀ የሥራ አካባቢ ማቅረብ ቁርጠኛ የሆንንበት ጉዳይ ነው፣ የኮንትራት ሰራተኞች እና ጎብኚዎች ሁሉንም ተፈጻሚነት ያላቸውን የጤና እና የደህንነት አጠባበቅ ሕጎች እና ደንቦች ያከብራሉ። የእኛን “BSafe!” የደህንነት አሰዳደር ማዕቀፍ አዘጋጅተናል። ይህ ማዕቀፍ የማይቋረጥ መሻሻልን ለማበረታታት፣ የተገኙ ትምህርቶችን ለማስተላለፍ፣ እንዲሁም የደህንነት አጠባበቅ ባህልን ለማጠናከር የተዘጋጀ የሥራ ሂደት ሲሆን፣ የሥራ አካባቢ ባሕርያትን እና ልማዶችን በማስተዳደር፣ በሥራ ቦታ የሚደርሱ ጉዳቶች እና ሕመሞች ስጋቶችን መቀነስ እንችላለን።

ማዕቀፎች፣ ሥርዓቶች እና የቁጥጥር ሥርዓቶች እንዳሉን ብናውቅም፣ እኛ ሁላችንም በአንድነት ደህንነቱ የተጠበቀ የሥራ ቦታ ለመፍጠር ኃላፊነት አለብን - ይኸም የማምረቻ ተቋሞቻችንን፣ የአገልግሎት ማዕከሎቻችንን እና ቢሮዎቻችንን ያካትታል።

# ለሰራተኞቻችን እና ለደህንነታቸው ዋጋ እንሰጣለን

የሥራ አካባቢ የአደጋ ስጋቶችን እና ለደህንነት አስጊ የሆኑ ባሕሪዎችን ለመቀነስ፣ የጤና እና የደህንነት አጠባበቅ መመሪያዎችን ማክበርና የሥራ ሂደቶቻችንን መከተል አለብዎ። ማናቸውንም የአደጋ ስጋቶች ከተመለከቱ ወዲያውኑ ለቅርብ ኃላፊዎ ይንገሩ። እንዲህ አይነቱ ሪፖርት ለክስተቶች ምላሽ ለመስጠት እና ከእነርሱም ትምህርት ለመውሰድ ይረዳናል።

**ተያያዥ ፖሊሲ፦**

<u>ጤና እና የደህንነት አጠባበቅ ፖሊሲ</u>

## እኛ ምን ማድረግ እንችላለን?

*አሰቸኳይ ሥራ በሥራ ቦታ ይፈለጋል። በአካባቢ የሚገኝ ኮንትራክተር ለመርዳት በአጭር ጊዜ ማሳወቂያ ተገኝቷል። ሥራው ያሉበት ስጋቶች ያልተመዘኑ ቢሆኑም እንኳ ያንን ሰው ማስገባት እንችላለን?*

አንችልም። የውስጥ የጤና እና የደህንነት አጠባበቅ የሥራ ሂደቶችን እና የአሰራር ሥርዓቶችን መከተል አለብን፣ እነዚህም ደህንነታቸው የተጠበቁ የአሰራር ዘዴዎችን ለማረጋገጥ የሚደረጉ የስጋት ምዘናዎችን ያካትታሉ። ከዚህም በተጨማሪ፣ የኮንትራት ሰራተኞች በርካታ መስፈርቶችን ግምት ውስጥ በሚከተው የምልመላ ፖሊሲዎች መሰረት መመረጥ አለባቸው፣ ይኸም ሰራተኞቹ ሥራውን ለመስራት አስፈላጊው ፈቃድ ያላቸው መሆኑን ማርጋገጥን ያካትታል።





ዓላማችን እና ዋነኛ እሴቶቻችን | የንግድ ሥራን በትክክለኛው መንገድ መሥራት | ለሰራተኞቻችን እና ለደህንነታችው ዋጋ እንሰጣለን | ሥራዎቻችንን በሥነ ምግባር እና በሐቀኝነት እንሠራለን | የንግድ ሥራችንን እንከላከላለን | ለአካባቢያችን እና ለማኅበረሰቦች እንጨነቃለን | የመረጃ ምንጮች

# ለሰራተኞቻችን እና ለደህንነታቸው ዋጋ እንሰጣለን

## በሥራ ላይ ያሉ መሠረታዊ መብቶች

International Labour Organisation (“ILO”) (የዓለማቀፍ የሥራ ድርጅት (“ILO”)) የመሠረታዊ የሥራ ላይ መርኆዎች እና የሥራ ላይ መብቶች፣ እንዲሁም የILOን የበርካታ አገር ኢንተርፕራይዞች እና ማኅበራዊ ፖሊሲን የሚመለከቱ የሶሰትዮሽ መርኆዎች አዋጆች እናከብራለን። ከሌሎችም በተጨማሪ፡በእነዚህ መርኆዎች መሠረት፣ የመሰብሰብ እና በአንድነት የመደራደር ነጻነትን በውጤታማነት እውቅና መስጠት፣ ማናቸውንም አይነት በግዳጅ የማሰራት ልማዶች ማስቀረት፣ የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛን በውጤታማነት ማስቀረት፣ እንዲሁም የሥራ ቅጥር እና ምደባን በተመለከተ አድልዎን ማስቀረት። የሥራ አካባቢዎቻችን፣ ደምወዞች እና ሌሎች የደመወዝ ክፍያዎች ሁሉንም አግባብነት ያላቸው ሕጎች እና ደንቦች ያከብራሉ እንዲሁም ከዓለማቀፍ የሥራ ደንቦች ጋር የተሰማሙ ናቸው።

**ተያያዥ ፖሊሲ፦**

<u>የሥራ ቅጥር ፖሊሲ</u>

ሠራተኞች በሥራ ቦታቸው ላይ እራሳቸውን እንዲያበለጽጉ እናበረታታለን፣ እንዲሁም ለሁሉም ሰራተኞች ተገቢውን ልማት እና ሥልጠና እናቀርባለን።

# ለሰራተኞቻችን እና ለደህንነታቸው ዋጋ እንሰጣለን

## ብዝኀነት፣ እኩልነት እና አካታችነት

እንደ ዘር፣ ቀለም፣ ኃይማኖት፣ ጾታ፣ የትውልድ አገር፣ የትውልድ ሃረግ፣ እድሜ፣ የአካል ጉዳት፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ወይም ጾታዊ ዝንባሌ የመሳሰሉትን ግምት ውስጥ ሳናስገባ ለሁሉም አመልካቾች እና ሰራተኞች እኩል የቅጥር ዕድል እንፈጥራለን። ሁሉም የቅጥር ውሳኔዎቻችን የሚመሰረቱት ተቀባይነት ያላቸው መስፈርቶች፣ ማለትም በክህሎት፣ የትምህርት ዝግጅት፣ የአፈጻጸም ብቃት፣ እና በንግድ ሥራው ፍላጎቶች ላይ በመመሰረት ነው።

ብዝኀነት፣ እኩልነት እና አካታችነትን የሚያበረታታ የሥራ አካባቢ መሆኑን ለማረጋገጥ ቁርጠኞች ነን።

**ተያያዥ ፖሊሲ፦**

[የሥራ ቅጥር ፖሊሲ]

## መከባበር ያለበት የሥራ አካባቢ

የሥራ አካባቢያችን ሁሉም ሰው የሚከበርበት እና ዋጋ የሚሰጠው ቦታ መሆን አለበት። የአፈጻጸም ብቃትን፣ የቡድን ሥራን፣ እና ውጤትን በግልጽ የመረጃ ልውውጥ አማካኝነት እናበረታታለን። "ሁሉን የሚያስተናግድ" የአስተዳደር ፖሊሲን እንደግፋለን፣ ስለሆነም ከሥራ ጋር ተያያዥ የሆኑ ስጋቶችን ለቅርብ ኃላፊዎ እንዲነግሩ ይበረታታሉ።

ለብዝኀነት፣ እኩልነት እና አካታችነት ባለን ቁርጠኝነት መሠረት፣ ማንኛውንም አይነት አድልዎ አንታገስም። እርሰዎ በፍጹም በአድሏዊ ድርጊት ውስጥ መገኘት፣ ወይም ያለ በቂ ምክንያት ሌሎችን በመገለጫ ባህሪዎቻቸው ላይ በመመሰረት በልዩ ሁኔታ ማስተናገድ የሚያስተናግዱበት ድርጊት መፈጸም የለብዎትም።





ዓላማችን እና ዋነኛ እሴቶቻችን | የንግድ ሥራን በትክክለኛው መንገድ መሥራት | ለሰራተኞቻችን እና ለደህንነታችው ዋጋ እንሰጣለን | ሥራዎቻችንን በሥነ ምግባር እና በሐቀኝነት እንሠራለን | የንግድ ሥራችንን እንከላከላለን | ለአካባቢያችን እና ለማኅበረሰቦች እንጨነቃለን | የመረጃ ምንጮች

# ለሰራተኞቻችን እና ለደህንነታቸው ዋጋ እንሰጣለን

የሥራ አካባቢያችን ከሁሉም አይነት የማዋከብ ድርጊቶች ነጻ መሆን አለበት - ማንኛውንም አይነት በሌሎች ላይ የሚደርስን ጥቃት አንታገስም። ጥቃት፣ በሥራ አፈጻጸም ላይ ተጽዕኖ የሚፈጥር እና ከመደበኛ የሥራ ላይ ባህሪ ውጭ የሆነ የማስፈራራት፣ የመዳፈር፣ ወይም አመቺ ያልሆነ የሥራ አካባቢን የሚፈጥር የቃል፣ አካላዊ ወይም ዕይታዊ ተግባርን ያካትታል። በአካላዊ እይታ ኃይማኖታዊ ዕምነቶች፣ ወይም በሥነ-አዕምሮ ልዩነት ላይ የተመሰረቱ ስድብ አዘል አስተያየቶች። ጥቃት ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ ይሚክተሉትን ሊያካትት ይችላል።ጾታዊ ይበላይነት፤በቃላት፤አካላዊ ንኪኪ፤ምቹ ያልሆነና ትብብር የሌለበት የሰራ ቦታ በመፍጠር ውጤታማነትና የስራ አፈጻጸም አሰቸጋሪ ያደርጋሉ።

አካላዊ ጥቃትን በተመለከተ የምንከተለው ትዕግሰት-አልባ ፖሊሲ ነው። አካላዊ ጥቃት፣ ሌላ ሰው ላይ አካላዊ ጥቃት ማድረስን፣ ጥፊ፣ መግፋት፣ ማስፈራራት፣ ወይም በሌላ ሰው ላይ ኃይል መጠቀም፣ ወይም የጦር መሣሪያዎችን መጠቅም፣ ወይም እነዚህን እንቅስቃሴዎችን እንደሚያደርጉ በመናገር ማስፈራራት ወይም በዚያ መሳተፍን ያካትታል። በማንኛውም አካላዊ ጥቃት እና ማዋከብ ድርጊት ላይ መሳተፍ የለብዎትም፣ እንዲሁም የማስፈራራት እና የጥቃት ቋንቋ መጠቀም የለብዎትም።

እንዲህ አይነት ባህሪዎች ካጋጠሙዎ ለቅርብ ኃላፊዎ፣ ለሰው ኃይል አስተዳደር ወይም Speak-Up Hotline መስመራችን በኩል መናገር ይችላሉ።

የማንታገሳቸው ባሕሪዎች፦

- አስጸያፊ ወይም ስሜት ጎጂ ቋንቋ
- ተገቢ ያልሆኑ አስተያየቶች ወይም ቀልዶች
- ስም ማጥፋት እና ሐሜት
- ወሲባዊ ትንኮሳዎች
- ያለ በቂ ምክንያት ሰራተኛን ከሥራ ገበታ ማግለል
- አንድን ሰው ዒላማ አድርጎ ሰውር ጥቃቶችን እና ማስፈራራቶችን መፈጸም

**ተያያዥ ፖሊሲ፦**

[የሥራ ቅጥር ፖሊሲ]

# ሥራዎቻችንን በሥነ ምግባር እና በሐቀኝነት እንሠራለን

ሁሉም ሰራተኞች በሥነ-ምግባር መርኆዎች መሠረት እና በከፍተኛ ሐቀኝነት እና ታማኝነት ሥራቸውን እንዲያከናውኑ እንጠብቃለን። ድርጊቶቻችን ግልጽ መሆን አለባቸው፡- ሐሳብን በመጠምዘዝ፣ በመደበቅ፣ ሚስጥራዊ መረጃን ያለአግባብ በመጠቀም፣ ያልሆነን ነገር እንደሆነ አስመስሎ በማቅረብ፣ ወይም በሌላ በማንኛውም ሚዛናዊ ያልሆነ ልማድ ማንኛውንም ሰው መጠቀሚያ አናደርግም።

ያሰቡት ተግባር ትክክለኛነት ላይ ጥርጣሬ ካደረብዎ፣ እባክዎ ምክር ይጠይቁ። የተሳሳተ የሚመስል ወይም ያን አይነት ስሜት የሚሰጥ ነገር ከተመለከቱ፣ ወዲያውኑ መናገር አለብዎ።

## ጉቦም ሆነ ሙስና አይፈቀድም

ጉቦ ማለት አንድ ሰው ያለ አግባብ ሚናቸውን በመጠቀም አንድ ነገር እንዲፈጽሙ ወይም አግባብነት ለሌለው የሥራ አፈጻጸም እውቅና ወይም ሽልማት ለማግኘት በማሰብ ዋጋ ያለው ነገር መስጠት ወይም መቀበል ነው። ጉቦዎች በርካታ አይነት መልኮች ይኖራችቸዋል፣ ስለሆነም ጥሬ ገንዘብ እና የጥሬ ገንዘብ ተመጣጣኞችን፣ ሥጦታዎችን፣ መዝናኛ፣ ብድሮች፣ ከሰዎች ጋር ለማገናኘት ቃል መግባትን፣ አገልግሎት ለመስጠት ቃል መግባትን፣ ወይም ፖለቲካዊ እና የልግሥና ስጦታዎችን ያካትታሉ።

ጉቦዎች፣ የማመቻቻ ክፍያዎችን፣ ማለትም የአንድን የመንግሥት የሥራ ሂደት ለማፋጠን በማሰብ ሕጋዊ መሠረት የሌላቸውና በመንግሰት ባለሥልጣናት የሚጠየቁ ትንንሽ ክፍያዎችን ወይም ተከፋዮችን ሊያካትት ይችላል። ሕገ ወጥ ኮሚሽን፣ ሌላኛው አይነት ጉቦ፣ በንግድ ሥራ ላይ ለሰሩት ውለታ ወይም ለሰጡት ድጋፍ ማካካሻ የሚከፈሉ ክፍያዎች ናቸው።



ማናቸውንም የጉቦ ወይም ሙስና አይነቶች አንታገስም፣ ስለሆነም ሁሉንም ተፈጻሚነት ያላቸው የጸረ-ጉቦ እና ሙስና ሕጎች ያክብሩ።





# ሥራዎቻችንን በሥነ ምግባር እና በሐቀኝነት እንሠራለን

ማናቸውንም አይነት ጉቦዎች በማንኛውም ቅርጽ መጠየቅ፣ መቀበል፣ ወይም መክፈል፣ የማመቻቻ ክፍያዎች ወይም ሕገወጥ ኮሚሽን በፍጹም መቀበል የለብዎትም።

በጉቦ ተግባር ውስጥ ለተሳተፋ የሶስተኛ ወገኖች ድርጊቶች እኛም በኃላፊነት ልንጠየቅ እንችላለን። እኛን በመወከል የሚንቀሳቀሱ ማናቸውም ኤጀንቶች፣ ወኪሎች ወይም አገናኞች ጉቦን እና ሙስናን ለመከላከል ያለንን ቁርጠኝነት የተረዱ መሆናቸውን ያረጋግጡ። ከእነዚህ ሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚሰሩ ጊዜ፣ አስፈላጊውን ማንነትን የማጣራት ሥራ መሥራት እና እኛን በመወከል ጉቦ የማይሰጡ ወይም ለመስጠት የማይደራደሩ መሆናቸውን ሁልጊዜ ማረጋገጥ አለብዎ።

ጉቦን እና ሙስናን ለመከላከል፣ ጉልህ ምልክቶችን መለየት መቻል አስፈላጊ ነው።

በተለይ እኛን በመወከል የሚንቀሳቀሱ ኤጀንቶች እና ሌሎች ሶስተኛ ወገኖችን በተመለከተ ጥንቃቄ ልናደርግባቸው የሚገቡ ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው፡-

- ከመጠን በላይ ከፍ ያሉ እና ፈቃድ ያልተሰጣቸው ኢንቮይሶች
- ለውጭ አገር የመንግሰት ባለሥልጣናት የሚከፈሉ ክፍያዎች
- ደጋፊ ሰነድ ሳይኖራቸው የሚፈጸሙ ክፍያዎች
- በሰራተኞች የሚከፈሉ አስፈላጊ ያልሆኑ ክፍያዎች

## ይህ መልካም ይሆን?

*አቅም ያለወ አቅራቢ ለእኛ አኩባንያ አገልግሎቶችን ማቅረብ ይፈልጋል። የእነርሱ ወኪል ለእኛ ሰራተኛ ለግል ፕሮጀክቶቹ ነጻ መሳሪያዎችን እንደሚሰጠው ቃል ይገባል። በምትኩ፣ እጩ አቅራቢው ከአርዳ ጋር የሚሰራ ሥራ እንዲሰጠው ይጠይቃል። ይህ መልካም ነው?*

አይደለም፣ ለሰራተኛው ቃል የተገቡለት መሳሪያዎች ጉቦ ናቸው። ሰራተኛው ግብዣውን እምቢ ማለት እና ይህን ተግባር Group Legal & Compliance. ሪፖርት ማድረግ አለበት። ለእኛ ጉቦ በመክፈል ሥራ መቀበል የሚፈልጉ አቅራቢዎች ከሥነ-ምግባር ውጭ የሚሰሩ ሲሆን ከእነርሱ ጋር ሥራ መሰራት የለብንም።

**ተያያዥ ፖሊሲ፡-**

የጸረ-ጉቦ እና የጸረ-ሙስና ፖሊሲ

# ሥራዎቻችንን በሥነ ምግባር እና በሐቀኝነት እንሠራለን

## ስጦታዎች እና መስተንግዶ

አነስተኛ ስጦታዎችን መስጠት እና መስተንግዶ ማድረግ በንግድ ግንኙነቶች ውስጥ መልካም ግንኙነትን የዳብራሉ። ተቀባይነት ያላቸው ስጦታዎች እና መስተንግዶዎች፣ ሥራውን የሚጠቅሙ ከሆነና፣ ምክንያታዊ የንግድ ሥራ ዓላማ ያላቸው ከሆኑ፣ በተፈጸሙበት ሁኔታዎች ውስጥ ተገቢ ከሆኑ እና የመደበኛ የስጦታ አሰጣጥ ልማድ አካል ካልሆኑ፣ ከሥነ-ምግባር ውጭ ወይም ሕገ-ወጥ አይደሉም። ይሁን እንጂ፣ በአንዳንድ ሁኔታዎች ውስጥ ስጦታዎችን እና መስተንግዶን መስጠት እና መቀበል፣ በተለይም ስጦታዎቹ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው ከሆኑ፣ ዓላማቸው ያለ አግባብ የሥራ ላይ ውሳኔዎች ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር ከሆነ የሙስና ድርጊት እንደሆኑ ሊቆጠሩ ይችላሉ።

ከሥነ-ምግባር ውጭ የሆነ ድርጊት ስለመፈጸሙ ሊመጡ የሚችሉ ክሶችን ለማስቀረት፣ አንድን ስጦታ ከመስጠትዎ ወይም ከመቀበልዎ በፊት፦

- ዋጋው እና ድግግሞሹ በጥብቅ የተገደበ መሆኑን
- ከተለመዱ የንግድ ሥራ ልማዶች ጋር የሚስማማ መሆኑን
- በስጦታ እና የመስተንግዶ ፖሊሲ መሰረት ዋጋው የተፈቀደ መሆኑን
- በእኛ የስጦታዎች እና መስተንግዶ ፖሊሲ መሰረት አስፈላጊ ፈቃዶች ይሰጣሉ።





ዓላማችን እና ዋነኛ እሴቶቻችን | የንግድ ሥራን በትክክለኛው መንገድ መሥራት | ለሰራተኞቻችን እና ለደህንነታችው ዋጋ እንሰጣለን | ሥራዎቻችንን በሥነ ምግባር እና በሐቀኝነት እንሠራለን | የንግድ ሥራችንን እንከላከላለን | ለአካባቢያችን እና ለማኅበረሰቦች እንጨነቃለን | የመረጃ ምንጮች

# ሥራዎቻችንን በሥነ ምግባር እና በሐቀኝነት እንሠራለን

ለመንግስት ባለሥልጣናት የሚሰጡ ስጦታዎችን እና መስተንግዶን በተመለከተ ልዩ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል (ለምሳሌ በመንግስት የቁጥጥር መሥሪያ ቤቶች ውስጥ የሚሰሩ ባለሥልጣናት)፣ እንዲሁም እንዲህ አይነት ስጦታዎችን ወይም መስተንግዶን ከመስጠት ወይም ከመቀበል በፊት ከGroup Legal & Compliance. ፍቃድ ማግኘት ያስፈልጋል።

**ተያያዥ ፖሊሲ፦**

የስጦታዎች እና መስተንግዶ ፖሊሲ



### ይህ ይፈቀዳል?

*አዲስ አቅራቢ ወደ እነርሱ ተቋም ለእርስዎ እና ለቤተሰብዎ ምንም ክፍያ የማይፈጸምበት የሽርሽር ጉዞ ግብዣ ያቀርብልዎታል። መቀበል ይችላሉ?*

አይችሉም፣ ይህን ግብዣ መቀበል የለብዎትም፤ በሁሉም ሁኔታዎች ውስጥ እንደታየው የቤተሰብ አባላትን ያካተተ የሽርሽር ጉዞ ለሥራ ዓላማ አስፈላጊ ከሆነው ተግባር ያለፈ ይሆናል። አግባብ ያልሆነ ተግባር መስሎ ከሚታይ ሁኔታ ሁልጊዜም ቢሆን ይራቁ።

### ስጦታ መቀበል የሚችሉት መቼ ነው?

ለመቀበል የማይከብድዎ ዋጋው ዝቅተኛ ከሆነ፣ የማስታወሻ ስጦታ (ለምሳሌ ብዕር ወይም ትንሽ ብራንድ ያለበት እቃ)። ስጦታው ከልክ ያለፈ ወጪ የወጣበት ከሆነ ፤ ገንዘብ ወይም የገንዘብ ተመጣጣኝ ከሆነ (ለምሳሌ የስጦታ ቫውቸር) ወይም አግባብና ምክንያታዊ ላልሆነ ተግባር እንደ ክፍያ የቀረበ ከሆነ ሊቀበሉ አይገባም።

# ሥራዎቻችንን በሥነ ምግባር እና በሐቀኝነት እንሠራለን

## የጥቅም ግጭቶች

ሁላችንም የአርዳን ጥቅሞች በሚያስጠብቅ ሁኔታ መሥራት አለብን። በሥራ ላይ የምናሳልፋቸው ውሳኔዎች ባልተገቡ የግል ፍላጎቶች ላይ መመስረት የለባቸውም እንዲሁም ማንኛችንም የግል ፍላጎቶቻችን ሚዛናዊነታችንን እና ሥራችን ላይ ተጽዕኖ እንዲያሳድር መፍቀድ የለብንም።

የጥቅም ግጭት የሚፈጠረው የግል ወይም የፋይናንስ ፍላጎታችን፣ ወይም የቅርብ ዘመድ ወይም ጓደኛ ፍላጎቶች፣ ከአርዳ ጋር የሚገዳደሩ ወይም ያንን ምስል የሚሰጡ ሲሆኑ፣ ወይም በሌላ መልኩ በአርዳ ጥቅሞች ላይ ጣልቃ ሲገቡ ነው። ማንኛውም የጥቅም ግጭት ሚዛናዊነታችንን ሊያሳጣን ይችላል፣ በዚያውም ከሥራ ጋር ተያያዥ የሆኑ ውሳኔዎቻችን ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል። እንዲህ አይነቱ ግጭት፣ ወይም ግጭት መሳይ ነገር፣ መተማመንን ይቀንሳል እንዲሁም የእርሰዎንም የአርዳን መልካም ስም ሊጎዳ ይችላል። የግጥም ግጭት፣ እርሰዎ ዘመድዎ ወይም ጓደኛዎ፣ በአርዳ ውስጥ ባለዎ የሥራ ድርሻ አማካኝነት አግባብነት የሌለው የግል ጥቅም በሚቀበሉ ጊዜ የጥቅም ግጭት ሊፈጠር ይችላል። ይህ በተለይ አሳሳቢ የሚሆነው እርሰዎ፣ በሥራ ድርሻዎ አማካኝነት ብድር፣ የግዳጅ ዋስትናን የሚቀበሉ ከሆነ ነው።

የጥቅም ግጭት ሊሆኑ የሚችሉ ሁኔታዎችን መለየት እና ማስቀረት አለብዎ። የጥቅም ግጭቶች በተለያየ መልኩ ይከሰታሉ፣ እናም ከቤተሰብ አባልዎ ጋር የአለቃነት ግንኙነት ካለዎ፣ ሸቀጦችን እና አገልግሎቶችን ከቅርብ ዘመድ መግዛት፣ ወይም ከሥራዎ ጋር የሚጋጭ የውጭ ሥራ ላይ መሰማራት። አንድን ግጭት በሚያውቁ ጊዜ፣ Group Legal & Compliance መገለጽ አለበት።

**ተያያዥ ፖሊሲ:-**

[የጥቅም ግጭቶች ፖሊሲ]

### የቤተሰብ ጉዳዮች?

*ትንሹ ወንድምዎ አርዳ ውስጥ እንዲሰራ ተቀጥሯል፣ እናም የእርሰዎ ቡድን ውስጥ ተመድቧል። ይህ ችግር የለውም፣ ወይስ አንድ ነገር ማለት ይጠበቅብዎታል?*

መናገር አለብዎ። ዘመድዎ ለእርሰዎ ሪፖርት ማድረጉ የጥቅም ግጭት ነው፤ እናም ከሌሎች ሰራተኞች ይልቅ እርሱን በልዩ ሁኔታ እንደሚያስተናግዱት ግምት ሊወሰድ ይችላል።



ዓላማችን እና ዋነኛ እሴቶቻችን | የንግድ ሥራን በትክክለኛው መንገድ መሥራት | ለሰራተኞቻችን እና ለደህንነታችው ዋጋ እንሰጣለን | ሥራዎቻችንን በሥነ ምግባር እና በሐቀኝነት እንሠራለን | የንግድ ሥራችንን እንከላከላለን | ለአካባቢያችን እና ለማኅበረሰቦች እንጨነቃለን | የመረጃ ምንጮች

# ሥራዎቻችንን በሥነ ምግባር እና በሐቀኝነት እንሠራለን

## የኮርፖሬት መልካም ዕድሎች

ለአርዳ በሚሰሩበት ወቅት፣አርዳ የመያዝ ፍላጎት ያሳደረበት የንግድ ወይም የኢንቨስትመንት መልካም ዕድል ሊለዩ ይችላሉ። እንዲህ አይነት የኮርፖሬት መልካም ዕድሎች በሚያግጥም ጊዜ፣ ሁሉም ግለሰቦች፣ ዳይሬክተሮችን እና መኮንኖችን ጨምሮ፣ የአርዳን ተቀባይነት ያለው ጥቅም የማስፈጸም ኃላፊነት ያለባቸው ሲሆን፣ የሚከተሉትን ከማድረግ ይከለከላሉ፦

- የአርዳን ንብረት፣ መረጃ ወይም የእርሰዎን የሥራ ድርሻ በመጠቀም የተገኙ ዕድሎችን እርሰዎ በግል መውሰድ;
- የአርዳን ንብረት፣ መረጃ ወይም የእርሰዎን የሥራ ድርሻ ለግል ጥቅም ማዋል እና
- ከአርዳ ጋር መገዳደር።

## ትክክለኛ የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ

ሁሉንም የንግድ ልውውጦች በትክክል፣ በሙሉ እና በወቅቱ የመመዝገብ ኃላፊነት አለብን። በማናቸውም የኩባንያ መዝገቦች ውስጥ የሐሰት፣ ወይም የፈጠራ ግብይቶችን መመዝገብ የለብዎትም፣ እንዲሁም የገቢም ሆነ የወጪ ሪፖርቶችን የእውነተኛው ዋጋ ከፍ ወይም ዝቅ አድርገው አያቅርቡ። የሐሰት መረጃ ሪፖርት ማድረግ በጥብቅ የተከለከለ ሲሆን፣ ለእርሰዎም ሆነ



የሒሳብ መግለጫዎቻችን የንግድ ሥራችንን የፋይናንስ ሁኔታ በሚዛናዊነት እና በትክክል ማንጸባረቅ አለባቸው።

# ሥራዎቻችንን በሥነ ምግባር እና በሐቀኝነት እንሠራለን

ለኩባንያችን ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል። የአርዳን አግባብነት ያለው የፋይናንስ ሁኔታ ሪፖርት ማድረግ፣ እያንዳንዳችን ያሉብን ኃላፊነቶች ወሳኝ ባህሪ ነው። የሐሰት መረጃ ሪፖርት ማድረግ በጥብቅ የተከለከለ ነው። (የዩኤስ የሰነድ መዋዕለ-ንዋይ እና ግብይት ኮሚሽን ን ጨምሮ) ለተቆጣጣሪ አካላት የሚገቡ፣ የሚላኩ ሪፖርቶች እና ሰነዶች እንዲሁም ለሕዝብ ይፋ የሚደረጉ መረጃዎች የተሟላ፣ ሚዛናዊ፣ ወቅታዊ እና ለመረዳት ቀላል የሆነ መግለጫን የማዘጋጀት ኃላፊነት አለብን።

የንግድ ሥራችንን ለመጠበቅ ያስቀመጥናቸውን የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቶቻችንን መከተል የእኛ የሁላችንም ኃላፊነት ነው። እነዚህ የቁጥጥር ሥርዓቶች በምንም አይነት መልኩ በአቋራጭ ሊኬድባቸው አይገባም። በተጨማሪም የእኛን የኦዲት ሥራ ወይም የሂሳብ መግለጫዎቻችንን ወይም የንግድ ሥራችንን እንዲገመግም የተመደበን የሂሳብ ባለሙያን (ውስጣዊም ሆነ የውጭ የሂሳብ ሰራተኛ) ማስገደድ፣ ማሳሳት፣ ወይም በሌላ መልኩ ማጭበርበር አይቻልም።

ይህን ጉዳይ በተመለከተ፣ አግባብነት የሌለው ተግባር መፈጸሙን ካወቁ ወይም ምልክቶችን ከተመለከቱ፣ መናገር አለብዎ።

**ተያያዥ ፖሊሲ፦**

የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብ ፖሊሲ

የሚከተሉትን በማድረግ የንግድ ሥራችንን ደህንነት እንጠብቃለን፦

- ሪፖርቶችን በሐቀኝነት እና በወቅታዊነት በማስገባት
- ትክክለኛ የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ መዝገቦችን በማዘጋጀት
- የንግድ እንቅስቃሴ መዝገቦችን ይዞ በማቆየት ፖሊሲዎቻችን መሰረት በማቅረብ
- ከውስጣዊ እና ውጫዊ ኦዲቶች ጋር ሙሉ በሙሉ በመተባበር

## ምን ማድረግ ይገባቸዋል?

*አንድ የፋይናንስ ኃላፊ፣ በክፍላቸው የሩብ ዓመት ሪፖርት ላይ ከተለመደው ወጣ ያሉ ነገሮችን ተመለከተ። ምን ማድረግ ይገባቸዋል?*

ሪፖርቶቹን በተቻለ ፍጥነት ማረም አለባቸው። ከተለመደው የወጡት ነገሮች መለወጥ ካልቻሉ፣ ማጭበርበር ተከስቶ ሊሆን ይችላል። በተቻለ ፍጥነት መናገር ያስፈልጋቸዋል። ለፋይናንስ ቡድን አባል ስጋታቸውን መግለጽ ይችላሉ። በተጨማሪም Speak-Up Hotline በመጠቀም፣ በምስጢራዊነት እና ማንነታቸዋን ሳያሳውቁ ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ።






# ሥራዎቻችንን በሥነ ምግባር እና በሐቀኝነት እንሠራለን

## የውስጥ የአክሲዮን ግብይት

አርዳን ወይም የንግድ ሥራ አጋሮቻችን የሆኑ ሌሎች ኩባንያዎችን በተመለከተ፣ ከንግድ ሥራችን ውጭ ለሆኑ ሰዎች ሊገኙ የማይችሉ አንዳንድ ምስጢራዊ መረጃ ሊያገኙ ይችላሉ። "ጉልህ ይፋዊ-ያልሆነ መረጃ" ወይም "የውስጥ መረጃ" የተሰኘውን እንዲህ አይነቱን መረጃ፣ የአክሲዮን ግብይትን ጨምሮ፣ ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት ሲሉ መጠቀም የለብዎትም። ይህ መረጃ የኩባንያውን የድርሻ ዋጋ ላይ፣ ወይም በሌሎች የኢንቨስትመንት ዕድሎች ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር ከሆነ የአርዳ የሰነድ መዋዕለ-ንዋይን ( የArdagh Metal Packaging S.A. አክሲዮኖችን ጨምሮ)፣ እና የሌሎች ኩባንያዎችን የሰነድ መዋዕለ ንዋይንም ያካትታል።

እኛ ሁላችንም የንግድ ሥራ መረጃን ምስጢራዊነት የመጠበቅ እና ለማንኛውም ከፍተኛ ዋጋ ያለው ለሕዝብ ይፋ ያልተደረገ መረጃን ለእራስዎ፣ ለቤተሰብዎ ወይም ለጓደኖችዎ የግል ጥቅም ላለማዋል ኃላፊነት አለብን። በውስጥ የአክሲዮን ግብይት ፖሊሲያችን መሰረት ከፍተኛ ዋጋ ያለው ለሕዝብ ይፋ ያልተደረገ መረጃ ካለዎ፣ ያ መረጃ ለሕዝብ ይፋ እስከሚሆን እና በገበያው ውስጥ እስኪሰርጽ ድረስና ከፍተኛ ዋጋ ያለው መሆኑ እስከሚያበቃ ድረስ ግብይት መፈጸም የለብዎትም።

ከፍተኛ ዋጋ ያለው ለሕዝብ ይፋ ያልሆነ መረጃን በመጠቀም የሰነድ መዋዕለ ንዋይ ግብይት ማድረግ ሕገወጥ ሲሆን፣ የተሳተፉ ግለሰቦች ለእስር ሊዳረጉ ይችላሉ።



# ሥራዎቻችንን በሥነ ምግባር እና በሐቀኝነት እንሠራለን

ይህ ለባለቤትዎ፣ ለአጋርዎ፣ ለጥገኛ የቤተሰብ አባሎችዎ እና ከእርስዎ ጋር ለሚኖሩ ሌሎች ሰዎችም ይሰራል።

በውስጥ የአክሲዮን ግብይት ፖሊሲ መሰረት፣ ተቀባይነት ያለው የሥራ ምክንያት ከሌለዎ በስተቀር ለማንኛውም ሰው፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከፍተኛ ዋጋ ያለው ለሕዝብ ይፋ ያልተደረገ መረጃን መግለጽ የለብዎትም (“ፍንጭ መስጠት” ይባላል)።

ቀጣይነት ባለው መልኩ ከፍተኛ ዋጋ ያለው ለሕዝብ ይፋ ያልሆነ መረጃ የሚያገኙ ከሆነ፣ ይህን ከመሰለው መረጃ ጋር በተያያዘ ተጨማሪ ገደቦች ይኖሩብዎታል። አንድ መረጃ ከፍተኛ ዋጋ ያለው ለሕዝብ ይፋ ያልሆነ ስለመሆኑ ማናቸውም ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎ የኩባንያውን ጸሐፊ ያነጋግሩ።

ከፍተኛ ዋጋ ያለው ለሕዝብ ይፋ ያልሆነ መረጃ ማለት ለሕዝብ ይፋ ያልተደረገና አንድ ምክንያታዊ ኢንቨስተር እነዚያን የሰነድ ማዋዕለ ንዋያት ለመግዛት፣ ለመያዝ ወይም ለመሸጥ መወሰን አስፈላጊ መሆኑን እንዲያስብ የማድረግ ጠባይ ያለው መረጃ ነው።

ከፍተኛ ዋጋ ያለው ለሕዝብ ይፋ ያልሆነ መረጃ ለምሳሌ፡-

- ይፋ ያልተደረጉ የፋይናንስ ሪፖርቶች
- ይፋ ያልተደረጉ የውህደት፣ የድርጅት ግልጽ ወይም የማስወገድ ዕቅዶች
- የታቀዱ ነገር ግን ይፋ ያልተደረጉ የኮርፖሬት አመራር ለውጦች
- የታቀዱ፣ ነገር ግን ይፋ ያልተደረጉ የቁልፍ ምርቶች መግለጫዎች
- ገና ይፋ ያልተደረጉ ጉልህነት ያላቸው በሂደት ላይ ያለ የሕግ ሂደት ውጤቶች።

**ተያያዥ ፖሊሲ፡-**

<u>የውስጥ አዋቂ አክሲዮን ግብይት ፖሊሲ</u>



# ሥራዎቻችንን በሥነ ምግባር እና በሐቀኝነት እንሠራለን

## የውድድር እና የጸረ-ውድድር ሕጎች ተስማሚነት

በገበያ ውስጥ በታማኝነት እና በሚዛናዊነት መንቀሳቀሳችንን እናረጋግጣለን። ይህም ማለት እንደ ንግድ ሥራ የተወዳዳሪነት ብልጫ የምናገኘው ብቃት ባለው አፈጻጸም እንጂ ከሥነ-ምግባር ውጭ በሆነና ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ አይደ ለም።

በማንኛውም የጸረ-ውድድር ተግባር ውስጥ መሳተፍ የለብዎትም። ከተወዳዳሪ ጋር በማንኛውም የጸረ-ውድድር ስምምነት ወይም መግባባት ውስጥ መግባት የለብዎትም፣ ይኽም ዋጋ የመወሰን፣ ጨረታ የማጭበርበር፣ ምርት የመገደብ፣ ወይም ደንበኞችን ወይም ገበያ መጋራትን ያካትታል። ማናቸውንም ምስጢራዊ የሆኑ የንግድ መረጃዎችን፣ ስለ ዋጋችን፣ ወጪያችን፣ ወይም ስትራቴጂያችን ለተወዳዳሪዎች አያጋሩ። ሥራዎ የውድድር መረጃ ሰብሰባን የሚያካትት ከሆነ፣ ይህን ማድረግ ያለብዎ በሕጋዊ መንገድ እና ጸረ-ውድድር በሆነ ዘዴ መሆን የለበትም። ኮንፈረንሶችን፣ የንግድ ትርዒቶችን ወይም የኢንዱስትሪ ማኅበራት ላይ በሚገኑ ጊዜ ከጸረ-ውድድር ተግባሮች ለመራቅ ልዩ ጥንቃቄ ማድረግ አለብዎ።

ንግድን በማደናቀፍ ላይ እየተሳተፉ እንደሆነ ከሚያስመስሉ ድርጊቶችም ጭምር መራቅ አለብዎ። በጸረ-ውድድር ሴራ ውስጥ እንዲሳተፉ ለማግባባት ሰዎች የቀረቡዎ ከሆነ፣ ወዲያውኑ እንደማይቀበሉ ይንገሯቸው፣ በሕገወጥ ተግባሩ ውስጥ መሳተፍ እንደማይፈልጉ በግልጽ ይንገሯቸው፣ ከዚያም Group Legal & Compliance. አባል ያሳውቁ።

**ተያያዥ ፖሊሲ፡-**

<u>የውድድር ተስማሚነት ፖሊሲ</u>

### ይህ መልካም ነው?

*የንግድ ትርዒት ላይ በሚገኙ ጊዜ፣ ከተወዳዳሪ ድርጅት የመጡ ሰራተኛ ወደ እርስዎ ቀረቡ። የግብዓት ዋጋዎች በመጨመራቸው ምክንያት እየገጠማቸው ስላለው ተግዳሮት መናገር ጀመሩ። እርስዎም የዋጋ ጭማሪውን ወደ ደንበኞቻችን ለማስተላለፍ ብትስማሙ ለገበያው ጠቃሚ እንደሚሆን ነገሩዎት። ምን ማድረግ አለብዎ?*

በዋጋ ላይ ስምምነት ለመፍጠር የቀረበልዎን ምክር ወዲያውኑ እና በግልጽ ውድቅ ማድረግ አለብዎ። እንዲህ አይነቱ ስምምነት ጸረ-ውድድር ሲሆን እኛ ሥራችንን የምንሰራበት መንገድ አይደለም። ውይይቱን በተመለከተ Group Legal & Compliance ያሳውቁ ተወዳዳሪዎች በሚገኙባቸው የንግድ ትርዒቶች ላይ ሲገኙ በተለይ ልዩ ጥንቃቄ ማድረግን አይርሱ።

# ሥራዎቻችንን በሥነ ምግባር እና በሐቀኝነት እንሠራለን


## ማዕቀቦች እና ወደ ውጭ የመላክ ክልከላ ሕጎች

በማናቸውም ድንበር ተሻጋሪ ግብይቶች ላይ ኃላፊነት ካለብዎ ወይም ከተሳተፉ፣ ለእኛ ንግድ ተፈጻሚ የሚሆኑ ደንቦችን ማወቅዎን ያረጋግጡ። እነዚህን ሕጎች አለማክበር በግንዳችን እና በመልካም ስማችን ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ሊኖረው ይችላል። እርስዎ ኃላፊ በሆኑበት አካባቢ ተፈጻሚ በሚሆኑ ሕጎች ላይ ማናቸውም ጥያቄዎች ካሉዎት Group Legal & Compliance ይጠይቁ።

**ተያያዥ ፖሊሲ፦**

ማዕቀቦች እና ወደ ውጭ የመላክ ክልከላ ሕጎች






ሁሉንም የንግድ ሕጎች እና ደንቦች፣ ማለትም የገቢ እና ወጪ ንግዶች ሕጎችን እንዲሁም የንግድ ማዕቀቦችን እናከብራለን።



ዓላማችን እና ዋነኛ እሴቶቻችን | የንግድ ሥራን በትክክለኛው መንገድ መሥራት | ለሰራተኞቻችን እና ለደህንነታችው ዋጋ እንሰጣለን | ሥራዎቻችንን በሥነ ምግባር እና በሐቀኝነት እንሠራለን | የንግድ ሥራችንን እንከላከላለን | ለአካባቢያችን እና ለማኅበረሰቦች እንጨነቃለን | የመረጃ ምንጮች

# የንግድ ሥራችንን እንጠብቃለን

ንብረቶቻችን ሥራችንን በየቀኑ የሚደግፉ የንግድ ሥራችን መሠረቶች ናቸው። ንብረቶቻችን ሰንል ቁሳዊ ንብረቶቻችንን (ሕንጻዎችን፣ መገልገያዎችን፣ ማሽኖችን፣ ተሽከርካሪዎችን እና ምርቶችን ጨምሮ)፣ የመረጃ ቴክኖሎጂ ሥርዓታችን፣ መረጃችን (ምስጢራዊ መረጃዎች እና የአሰራር እውቀቶች እና የመረጃ ቴክኖሎጂ ሥርዓቶች) ያካትታል።

## ማጭበርበርን መከላከል

በሐቀኝነት ለመሥራት እንደገባንበት ቁርጠኝነት አንድ አካል - ድርጊቱ የተፈጸመው በሰራተኛም ሆነ በማንኛውም ሦስተኛ ወገን የሚፈጸም ማንኛውንም ማጭበርበር እንታገሰም። ማጭበርበር ማለት ያልተገባ ወይም ሕገወጥ ጥቅም ለማግኘት ሲባል ሆን ብሎ ለማሳሳት ወይም ለማታለል የሚገባ ነገርን ያለማድረግ ተግባር ነው። ማጭበርበር ያልተፈቀደ የንብረት አጠቃቀምን፣ የውሸት የሂሳብ አያያዝ ወይም የፋይናንስ ሪፖርት ማድረግን፣ የግብር ማጭበርበርን፣ ማስመሰልን ወይም የንብረት አለአግባብ መጠቀምን ሊያካትት ይችላል። በንግድ ሥራችን ውስጥ ሁላችንም ማጭበርበርን መከላከል ኃላፊነታችን ነው።

**ተያያዥ ፖሊሲ፦**

የጸረ-ማጭበርበር ፖሊሲ



ሁላችንም የንግድ ሥራችንን እና ንብረቶቻችንን የመጠበቅ እና ደህንነታቸው እንደተጠበቀ የማቆየት ኃላፊነት አለብን።

# የንግድ ሥራችንን እንከላከላለን

## ተጨባጭ ንብረቶቻችንን ደህንነት መጠበቅ

እያንዳንችን የአርዳን ንብረቶች ከጉዳት፣ ከብክነት፣ ከአላጋግባብ መጠቀም እና ከስርቆት የመከላከል ኃላፊነት አለብን። በሁሉም አካባቢዎቻችን፣ የማምረቻ ተቋሞቻችንን፣ የአገልግሎት ማዕከላትን እና ቢሮዎችን ጨምሮ የአካባቢን ደህንነት የመጠበቅ ኃላፊነት አለብን። ወደ አካባቢያችን የሚገባው ለተፈቀደላቸው ሰዎች ብቻ መሆን አለበት። እዚያ መገኘት የሌለበትን ሰው እዚያ ካዩ፣ መናገር አለብዎ።

በተጨማሪም ንብረቶቻችንን ለተፈቀደላቸው ዓላማዎች እና በአግባቡ መጠቀማችንን ማረጋገጥ አለብን።

**ተያያዥ ፖሊሲ፦**

<u>የአካባቢ ደህንነት ፖሊሲ</u>

## ምን ማድረግ አለብዎ?

*እርሰዎ ከሥራ ባልደረባዎ ጋር ነዎት፣ እናም በርካታ ሰዎች የደህንነት ጃኬቶችን ለብሰው በአንድ ላይ ሲራመዱ ያያሉ። ማንም ሰው ባጅ አላጠለቀም፣ እርሰዎም አያውቋቸውም። ብዙዎቹን የሥራ ባልደረባዎችዎን እንደሚያውቋቸው ያሰባሉ። ምን ማድረግ አለብዎ?*

አሰቁመዋቸው ማን እንደሆኑ እና ዓላማቸው ምን እንደሆነ፣ እንዲሁም በአካባቢው ላይ የተገኙበት ምክንያት ምን እንደሆነ በትህትና መጠየቅ አለብዎ።





ዓላማችን እና ዋነኛ እሴቶቻችን | የንግድ ሥራን በትክክለኛው መንገድ መሥራት | ለሰራተኞቻችን እና ለደህንነታችው ዋጋ እንሰጣለን | ሥራዎቻችንን በሥነ ምግባር እና በሐቀኝነት እነሠራለን | የንግድ ሥራችንን እንከላከላለን | ለአካባቢያችን እና ለማኅበረሰቦች እንጨነቃለን | የመረጃ ምንጮች

# የንግድ ሥራችንን እንከላከላለን

## ምስጢራዊ መረጃዎቻችንን መጠበቅ

ምስጢራዊ መረጃችን የንግድ ሥራችንን ደህንነት ለመጠብቀ መከላከል ያለብን ወሳኝ ንብረት ነው። ምስጢራዊ መረጃ፣ የአዕምሮ ንብረትን፣ የንግድ ምስጢርን፣ የአሰራር እውቀትን፣ የግል ውሂብን፣ እንዲሁም ስትራቴጂ እና የንግድ ሥራ ውሳኔዎችን ያካትታል።

ከአርዳ ውስጥም ሆነ በውስጥ ላሉ ማናቸውም ሰዎች፣ ካልተፈቀደ ወይም በሕግ እንደዚያ እንዲያደርጉ ካልተገደዱ በስተቀር፣ የትኞቹንም ምስጢራዊ መረጃዎቻችንን ለሌሎች መግለጽ የለብዎትም።

ምስጢራዊ መረጃ የሚከተሉትን ያካትታል፦

- ቴክኒካዊ መረጃ ወይም የአሰራር እውቀት
- አዕምሯዊ ንብረት
- የንግድ ምስጢሮች
- የወደፊት የምርት መረጃ
- የንግድ እና የስትራቴጂ ዕቅዶች
- ምስጢራዊ የግል መረጃ
- የግል መረጃ

ምስጢራዊ መረጃን በሚይዙ ጊዜ ልዩ ጥንቃቄ ማድረግ አለብዎ፣ ለምሳሌ ባለዎ የሥር ድርሻ የሚያስፈልግዎትን መረጃ ብቻ መውሰድ፣ እንዲሁም የመረጃን ደህንነት ለመጠበቅ ተገቢ የደህንነት እርምጃዎችን መውሰድ፤ እንዲሁም ማናቸውንም አጠራጣሪ የምስጢራዊ መረጃ ስርቆት ወይም አላግባብ አጠቃቀም ወዲያውኑ ሪፖርት ማድረግ አለብዎ።

**ተያያዥ ፖሊሲ፦**

<u>የውስጥ አዋቂ የአክሲዮ ግብይት ፖሊሲ</u>

## ይህ መልካም ነው?

*በማምረቻ ተቋማችን ውስጥ አዲስ የማስተዋወቂያ ማሽጊያ ዲዛይን ለአንዱ ደንበኞችን እያመረትን መሆኑን በመመልከትዎ ደስ አለዎት። ይህን ዜና ለጓደኞችዎ ማውራት ይችላሉ?*

ገና ይፋ ያልተደረገን ማንኛውንም መረጃ ከሥራ ቦታ ውጭ ማጋራት የለብዎትም። እኛ ወይም ደንበኞችን አዲሱን የማሽጊያ ዲዛይን ቀድሞ ይፋ አድርጎ ከሆነ፣ ዜናውን መንገር ይችላሉ። ያ ካልሆነ ግን፣ ይፋ እስከሚደረግ ድረስ ይቆዩ።

# የንግድ ሥራችንን እንከላከላለን

## የመረጃ ቴክኖሎጂ (IT) ሥርዓቶቻችንን መጠበቅ

ሥርዓቶቻችንን ለመንከባከብ እና በአግባቡ ለመጠቀም፣ እንዲሁም ደህንነታቸውን ለመጠበቅ እና ለማስጠበቅ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን። በIT መገልገያዎቻችን እና በሥርዓቶቻችን በሚሰሩ ጊዜ ፖሊሲዎቻችንን እና መመሪያዎቻችንን መከተል አለብዎ። የመረጃ ቴክኖሎጂ ሥርዓቶቻችንን አላግባብ አጠቃቀምን አንታገሰም።

መረጃ ሥርዓቶቻችንን፣ ሥርዓታችንን ለመጉዳት እና መረጃዎቻቸንን ለመስረቅ ከሚፈልጉ ጉዳት አድራሽ አጥፊዎች ለመከላከል ስለ መረጃ ቴክኖሎጂ በቂ እውቀት ያለን መሆን አለብን። ሥርዓቶቻችንን እና መረጃዎቻችንን ሁለቱንም ለመጠበቅ ተመራጭ ከሆኑ መንገዶች አንዱ ጠንካራ የይለፍ ቃላት መጠቀም እና ለማንም አለማጋራት ነው። ኢሜይሎችን በሚከፍቱ እና አገናኞችን በሞጎበኙ ጊዜ ጠንቃቃ መሆን አለብዎ፣ በተለይ በሞባይል መሳሪያ ላይ።



**ተያያዥ ፖሊሲ፦**

[የቡድን የሳይበር ጥበቃ ፖሊሲ]

[የቴክኖሎጂ ፖሊሲ]

ማናቸውንም ድብቅ እንቅስቃሴዎች ከተጠራጠሩ ለIT ደህንነት ቡድን ወዲያውኑ ያሳውቁ።

### ምን ማድረግ አለብዎ?

*አንድ አባሪ ምንም ችግር የለውም ብለው በማሰብ ጠቅ ያደርጋሉ፣ ከዚያም ወዲያውኑ ትክክለኛ አባሪ አለመሆኑን ይረዳሉ። ምን ማድረግ አለብዎ?*

ማናቸውንም ስጋቶች በተቻለዎ ፍጥነት ለIT  ደህንነት ቡድን ማሳወቅ አለብዎ።

በተለይ በኢሜይሎች ውስጥ አገናኞች ላይ ጠቅ በሚያደርጉ ጊዜ ልዩ ጥንቃቄ ማድረግ አለብዎ፣ ምክንያቱም ብዙውን ጊዜ በወንጀለኞች እና ወደ ሥርዓታችን ሰብረው መግባት በሚፈልጉ አጥፊዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ።



ዓላማችን እና ዋነኛ እሴቶቻችን | የንግድ ሥራን በትክክለኛው መንገድ መሥራት | ለሰራተኞቻችን እና ለደህንነታችው ዋጋ እንሰጣለን | ሥራዎቻችንን በሥነ ምግባር እና በሐቀኝነት እንሠራለን | የንግድ ሥራችንን እንከላከላለን | ለአካባቢያችን እና ለማኅበረሰቦች እንጨነቃለን | የመረጃ ምንጮች

# የንግድ ሥራችንን እንከላከላለን

## የመረጃ ግላዊነት

ሰራተኞችን እና ሶስተኛ ወገኖችን ጨምሮ፣ የሁሉንም ግለሰቦች ግላዊነት እናከብራለን፣ እንዲሁም ተፈጻሚነት ያላቸውን የውሂብ ግላዊነት ሕጎች ለማክበር ቁርጠኞች ነን። ሁላችንም አግባብነት ያላቸው የመረጃ ግላዊነት ሕጎችን የመረዳት እና የማክበር ኃላፊነት አለብን።

የግል መረጃን ማንኛውንም ማንነቱ ሊለይ የሚችል ግለሰብን የተመለከተ ውሂብን ይመለከታል፣ ለምሳሌ፣ ሰም፣ አድራሻ፣ መታወቂያ ቁጥር፣ እና የጤና መረጃ። ይህ ውሂብ በበርካታና የተለያዩ ቅርጸች፣ ለምሳሌ በወርቀት ሰነዶች፣ በኢሜይሎች፣ እና በኤሌክትሮኒክ እና ሌሎች ዲጂታል ሥርዓቶች ውስጥ ሊቀመጥ ይችላል። የግል መረጃን መሰብሰብ እና ማጋራት ያለብዎ ያንን ለማረግ ተቀባይነት ያለው የንግድ ምክንያት ካለዎ ብቻ፣ እንዲሁም በአካባቢው የውሂብ ግላዊነት ሕግ መሰረት መሆን አለበት።

የውሂብ ጥሰት እንዳለ ካወቁ፣ ወዲያውኑ ይህን ለGroup Legal & Compliance ሪፖርት ማድረግ አለብዎ።

ከውሂብ ግላዊነት ጋር ተያያዥ የሆኑ ማናቸውም ስጋቶች እና ጥያቄዎች Group Legal & Compliance. መመራት አለባቸው።

### ምን ማድረግ አለብዎ?

*ሰም፣ ኢሜይል አድራሻዎች፣ እና መታወቂያ ቁጥርን የያዘ ኢሜይል ለተሳሳተ ሰው በስህተት ላኩ። ምን ማድረግ አለብዎ?*

ይህ የውሂብ ጥሰት ሊሆን ይችላል። ወዲያውኑGroup Legal & Compliance. ማነጋገር አለብዎ። መረጃን በመመሰጠር እና ሰነዶችን በይለፍ ቃል በመጠበቅ የመረጃ ግላዊነትን ደህንነቱ ተጠብቆ ለመላክ ልዩ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን።

**ተያያዥ ፖሊሲ፦**

[የቡድን የውሂብ ግላዊነት ፖሊሲ]

# ለአካባቢያችን እና ለማህበረሰባችን እንጨነቃለን

ለአካባቢያችን እና ለማኅበረሰባችን መጠንቀቅ እና በምንሠራቸው ሥራዎች በዋነኝነት ግምት ውስጥ የምናስገባው ነገር ነው። ጤናማ እና ደህንነታቸው የተጠበቁ አካባቢዎችን እናበረታታለን፣ ዘላቂነት ያላቸው የሥራ ሂደቶችን እንዘረጋለን፣ እንዲሁም ከማኅበረሰባችን እና በአጠቃላይም ከኅብረተሰቡ ጋር እንዴት እንደምንገናኝ ዋጋ እንሰጣለን።

## ለአካባቢያችን ዋጋ መስጠት

ለአካባቢያችን ዋጋ እንሰጣለን፣ እንዲሁም ጥበቃ ለማድረግ ቁርጠኞች ነን። በመላው የንግድ ሥራችን ውስጥ ቀጣይነት ያለው የአካባቢ ጥበቃ አፈጻጸም እንዲኖር ለመትጋት ያለብንን ኃላፊነት እንገነዘባለን። አግባብነት ያላቸውን የአካባቢ ጥበቃ ሕጎች እና ደንቦች ለማክበር እና በተሰጠን የአካባቢ እና የክንውን ገደብ ውስጥ ለመሰራት ቁርጠኞች ነን።

በማምረቻ ተቋሞቻችን፣ አገልግሎት ማዕከሎቻችን እና ቢሮዎቻችን ውስጥ የአካባቢ ጥበቃ አስተዳደር ሥርዓቶችን በመዘርጋት መልካም የአካባቢ ጥበቃ ልማዶች እና ቀጣይነት ያለው መሻሻል መኖራቸውን በማረጋገጥ፣ በአካባቢው ላይ የሚኖረንን ተጽዕኖ ለመቆጣጠር ጥረት እናደርጋለን። ማናቸውንም አይነት ኅጂ የአካባቢ ጥበቃ ልማዶችን ከተመለከቱ መናገር አለብዎ።

**ተያያዥ ፖሊሲ፦**
የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲ

## ምን ማድረግ ይገባኛል?

*አንድ መገልገያ መሣሪያ አካባቢውን ሊበክል የሚችል ፈሳሽ እያንጠባጠበ እንደሆነ ተመልክተዋል። ምን ማድረግ አለብዎ?*

ማንኛውንም በሰው ላይ የጤና ጉዳት የሚያደርስ እና አካባቢን የሚበክል ሁኔታ በሚመለከቱ ጊዜ መናገር እና ሪፖርት ማድረግ አለብዎ።





ዓላማችን እና ዋነኛ እሴቶቻችን | የንግድ ሥራን በትክክለኛው መንገድ መሥራት | ለሰራተኞቻችን እና ለደህንነታችው ዋጋ እንሰጣለን | ሥራዎቻችንን በሥነ ምግባር እና በሐቀኝነት እንሠራለን | የንግድ ሥራችንን እንከላከላለን | ለአካባቢያችን እና ለማኅበረሰቦች እንጨነቃለን | የመረጃ ምንጮች

# ለአካባቢያችን እና ለማኅበረሰቦች እንጨነቃለን

## ዘላቂነት ላይ ማተኮር

በማኅበረሰባችን፣ እንዲሁም በአጠቃላይ በኅበረተሰቡ ዘንድ ዘላቂ አወንታዊ ተጽዕኖ ለመፍጠር ቁርጠኞች ነን። ለዘላቂነት የሚኖረን አቀራረብ ሙሉ በሙሉ ከንግድ ሥራችን ጋር የተዋሃደ እና በሶስት ዓምዶች ዙሪያ የተደራጀ ነው፦ ልቀቶች፣ ሥነ ምኅዳር፣ እና ማኅበራዊ ደህንነት ናቸው። ስትራቴጂያችንን እና ቃል ኪዳኖቻችንን፣ እንዲሁም በዘላቂነት ሪፖርቶቻችን ውስጥ እነዚያን ግቦች ለማሳካት የወሰድናቸውን እርምጃዎች ሰንደን እናስቀምጣለን። እነዚህ ሪፖርቶች፣ ከሌሎች ለዘላቂነት የምናደርጋቸውን ጥረቶች የተመለከቱ መረጃዎች ጋር ተዳምሮ፣ ድህረ ገጽ ላይ ይገኛል። የዘላቂነት ስትራቴጂያችንን እና ቃል ኪዳኖቻችንን ወደ ተግባር ለመለወጥ እንዴት እንደምንሰራ እንዲረዱ



በዕለት-ተዕለት እንቅስቃሴዎቻችን ውስጥ ዘላቂነት ያላቸው ልማዶችን ለመደገፍ ትንሽም ሆነ ትልቅ ሁላችንም እርምጃዎችን መውሰድ እንችላለን። በየዕለቱ ምን ማድረግ እንደምንችል አንዳንድ ምሳሌዎች እነሆ፦

- የመልሶ መጠቀም ጥረቶች ላይ ግንባር ቀደም መሆን
- ቆሻሻን መቀነስ እና በሚቻል ጊዜ ሁሉ ቁሳቁሶችን መልሶ መጠቀም
- ከክፍል ሲወጡ መብራት ማጥፋት
- በአገልግሎት ላይ ያልሆኑ መሳሪያዎችን መጥፋት እና ሶኬታቸውን መንቀል

# ለአካባቢያችን እና ለማህበረሰባችን እንጨነቃለን

ይበረታታሉ።

## ማኅበረሰቦቻችንን መደገፍ

በውስጣቸው የምንኖርባቸውን እና ሥራችንን የምናከናውንባቸውን ማኅበረሰቦች ለመደገፍ ቁርጠኞች ነን። ይኸን፣ እርስዎም እንዲሳተፉባቸው የሚበረታቱባቸው የማኅበረሰብ አሳታፊ ፕሮጀክቶችን ጨምሮ በተለያዩ መንገዶች እናከናውናለን። በ እርዳ ለትምህርት ፕሮግራማችን በኩል በኢንዱስትሪያችን ውስጥ ብዝኀነትን እናወድሳለን እንዲሁም ዝቅተኛ አገልግሎት የሚያገኙ ማኅበረሰቦችን እንደግፋለን። በዚህ ፕሮግራም አማካይነት ለተማሪዎች በሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ምሕንድስና፣ እና ሒሳብ (STEM) ትምህርት ላይ መዋዕለ ንዋይ እናፈስሳለን።

ድርጅታችን በሚመራበት <u>የእርዳታ አሰጣጥ ፖሊሲ</u>። መሠረት በማህበረሰቡ ውስጥ የሚገኙ ሃገር በቀል በጎ አድራጎት ድርጅቶችን ያግዛል። ለፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም እጩዎች ምንም አይነት አያደርግም።

**ተያያዥ ፖሊሲ፦**
<u>የእርዳታ አሰጣጥ ፖሊሲ</u>

### ምን ማድረግ አለብዎ?

*በአካባቢያዊ የማኅበረሰብ የግብረ ሰናይ ውስጥ ይሳተፋሉ። ደንበኞቻችንን እና አቅራቢዎቻችንን ግብረሰናዩን እንዲደግፉ መጠየቅ ይችላሉ?*

አይችሉም፣ ደንበኞችን እና አቅራቢዎችን የግል ግብረ ሰናይ እንቅስቃሴን እንዲደግፉ መጠየቅ አግባብነት የሌለው ተግባር ወይም የጥቅም ግጭት ይመስላል። ምናልባት የእርስዎ አካባቢያዊ ግብረ ሰናይ ከአካባቢያዊ የልገሳ በጀታችን ሊጠቀም ይችላል። እንዲህ አይነት ልገሳ የሚፈልጉ ከሆነ፣ ከአካባቢያዊው አስተዳደር ጋር መነጋገር ይችላሉ።

ስለ ማኅበረሰብ ፕሮጀክቶቻችን ወይም ስለ ግብረ ሰናይ ተግባር የበለጠ ማወቅ ከፈለጉ የዘላቂነት ቡድን አባልን ያነጋግሩ።



ዓላማችን እና ዋነኛ እሴቶቻችን | የንግድ ሥራን በትክክለኛው መንገድ መሥራት | ለሰራተኞቻችን እና ለደህንነታችው ዋጋ እንሰጣለን | ሥራዎቻችንን በሥነ ምግባር እና በሐቀኝነት እንሠራለን | የንግድ ሥራችንን እንከላከላለን | ለአካባቢያችን እና ለማኅበረሰቦች እንጨነቃለን | የመረጃ ምንጮች


# ለአካባቢያችን እና ለማኅበረሰቦች እንጨነቃለን

## በእሴት ሰንሰለታችን ውስጥ ሰብዓዊ መብቶችን ማክበር እንዲሁም የማኅበራዊ ኃላፊነቶች ማስተዋወቅ

የሰብዓዊ መብቶች ዓለማቀፍ አዋጆችን እናከብራለን እንዲሁም በንግድ ሥራችን እና በዓለማቀፍ የእሴት ሰንሰለታችን ውስጥ ሰብዓዊ መብትን ለማክበር ቁርጠኞች ነን። ደህንነቱ የተጠበቀ የሥራ ሁኔታ፣ የሰው ልጅ ብዝበዛን መከላከል፣ (የግዳጅ ሥራ፣ የሕጻናት ጉልበት እና ሕገወጥ የሰው ዝውውርን ጨምሮ)፣ አድልዎ፣ እና የአካባቢ ጥበቃ አስተዳደርን ከተመለከቱ የሰብዓዊ መብቶች ጋር ተያያዥ የሆኑ ሁሉንም ሕጎች እናከብራለን እንዲሁም አቅራቢዎቻችንም እንዲያከብሩ እንጠብቃለን።

በመላው የእሴት ሰንሰለታችን ማኅበራዊ ኃላፊነትን እናበረታታለን እንዲሁም የንግድ ሥራ በአጋርነት የምንሰራው በደንባችን ውስጥ የተቀመጡ መርኖዎችን እና እሴቶችን ከሚያከብሩ አጋሮች ጋር ብቻ ነው። ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በምንገናኝ ጊዜ፣ እነዚህን መርኖዎች እና እሴቶች፣ እንዲሁም ኃላፊነት የተሞላ የንግድ ፖሊሲያችንን ማክበር እንደሚጠበቅባቸው መገንዘባቸውን እና ማወቃቸውን ማረጋገጥ አለብዎ።

**ተያያዥ ፖሊሲ፦**
<u>የማኅበረሰብ ዘላቂነት ፖሊሲ</u>
<u>ኃላፊነት የተሞላ የንግድ ፖሊሲ</u>



# የመረጃ ምንጮች

| የመረጃ ምንጮች፡- | በሚከተለው ላይ እገዛ ለማግኘት፡- | የሚያነጋግሩት ሰው፡- |
|---|---|---|
| Group Legal & Compliance | ስለ ደንቡ ስጋቶች እና ጥያቄዎች | compliance@ardaghgroup.com |
| ለሰው ኃይል አስተዳደር | ከሰው ኃይል አስተዳደር ጋር ተያያዥ የሆኑ ስጋቶች ወይም ጥያቄዎች | የአካባቢዎ የሰው ኃይል አስተዳደር ኃላፊ |
| የግሩፕ ፋይናንስ | የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ፖሊሲ ወይም ጥያቄዎች | የአካባቢ ወይም የግሩፕ ፋይናንስ አባል |
| IT ደህንነት | የመረጃ ቴክኖሎጂ ደህንነትን የተመለከቱ ስጋቶች ወይም ጥያቄዎች፣ ወይም የመቴ ደህንነት አደጋን ሪፖርት ለማድረግ | AGGRP.ITSecurity@ardaghgroup.com |
| የመረጃ ግላዊነት | መረጃ ግላዊነትን ወይም መረጃ ጥሰትን የተመለከቱ ስጋቶች ወይም ጥያቄዎች፣ ወይም የውሂብ ጥሰትን ሪፖርት ለማድረግ | privacy@ardaghgroup.com |
| ዘላቂነት | ስለ ዘላቂነት ስትራቴጂያችን እና ቃል ኪዳኖቻችንን የተመለከተ መረጃ ወይም ዝርዝሮች | sustainability@ardaghgroup.com ardaghgroup.com/corporate/sustainability |
| የእኔ አርዳ | ፖሊሲዎች እና የውስጥ ሰነዶች የሚገኙበት አድራሻ | ardagh.sharepoint.com (የውስጥ መዳረሻ ብቻ) |





## Speak-Up Hotline
## ሪፖርት ማድረጊያ አማራጮች

### መስመር ላይ፡-

በድር በኩል ችግን ሪፖርት ለማድረግ እባክዎ የሚከተለውን ይጎብኙ፡- ardaghgroup.ethicspoint.com

### ስልክ፡-

ሪፖርት ማድረጊያ የቀጥታ ስልኮች ከታች ባለው ሰንጠረዥ ውስጥ በተጠቀሱ አገሮች ውስጥ ይገኛሉ።

በእርስዎ አገር የመደወያ ክልከላዎች ካሉ ማረጋገጥ አለብዎ።

እርስዎ የሚጠቀሙበት ስልክ ዓለማቀፍ ጥሪዎችን የማድረግ የሚችል መሆን አለበት።

ለአገርዎ የተጠቀሰውን ስልክ ቁጥር ይደውሉ እና፣ አግባብነት ካለው፣ የመዳረሻ ኮዱን ይደውሉ። እባክዎ ከታች የተገለጹት ሁሉም የቀጥታ መስመሮች በተጨማሪነት በእንግሊዝኛም እንደሚገኙ ይወቁ።

| አገር | ቋንቋዎች | ስልክ | የመዳረሻ ኮድ | ክልከላዎች |
|---|---|---|---|---|
| ኦስትሪያ | ጀርመንኛ | 0 800 200 288 | 855 344 1555 | ክልከላዎች የሉም |
| ብራዚል | ፖርቱጋልኛ | 0800 892 0780 | | ክልከላዎች የሉም |
| ዴንማርክ | ዴንማርክኛ | 080 25 15 34 | | ክልከላዎች የሉም |
| ኢትዮጵያ | አማርኛ | 800 861 957 | | ክልከላዎች የሉም |
| ፈረንሳይ | ፈረንሳይኛ | 0805 54 29 81 | | ክልከላዎች የሉም |
| ጀርመን | ጀርመንኛ | 0800 7241915 | | ክልከላዎች የሉም |
| አየርላንድ | እንግሊዝኛ | 1800 456762 | | ክልከላዎች የሉም |
| ኢጣልያ | ጣልያንኛ | 800 925 014 | | ክልከላዎች የሉም |
| ኬንያ | እንግሊዝኛ | 0800 221 363 | | ክልከላዎች የሉም |
| ኔዘርላንድስ | ደች | 0800 440 0006 | | ክልከላዎች የሉም |
| ናይጄርያ | እንግሊዝኛ | 855 344 1555 | 0 708 060 1816 | ክልከላዎች የሉም |
| ፖላንድ | ፖላንድኛ | 800 707 081 | | እባክዎ አንዳንድ አገልግሎት አቅራቢዎች ለነጻ የስልክ መስመር ክፍያ ሊጠይቁ እንደሚችሉ ይገንዘቡ |
| ሰርቢያ | ሰርቢያኛ | 0800 190 669 | | ሰርቢያ ITFS እና የሞባይል መስመር የሚገኘው በTelekom Serbia በኩል ብቻ ነው። |
| ደቡብ አፍሪካ | እንግሊዝኛ | 080 001 0398 | | ክልከላዎች የሉም |
| ስፔን | ስፔንኛ | 900 810 705 | | ክልከላዎች የሉም |
| ስዊድን | ስዊድንኛ | 020 10 92 18 | | ክልከላዎች የሉም |
| ስዊዘርላንድ | ጀርመንኛ | 0 800 890 | 855 344 1555 | ከሞባይል/ሴሉላር ስልኮች ይገኛል፣ ክፍያዎች ሊኖሩ ይችላሉ |
| ዩናይትድ ኪንግደም | እንግሊዝኛ | 08005873808 | | ለአይል ኦቭ ማን እና ጀርሲም ይሰራል |
| ዩናይትድ ስቴትስ | እንግሊዝኛ፣ ስፔንኛ | 855 344 1555 | | ክልከላዎች የሉም |

ardaghgroup.com

ArdaghGroup